STAY SAFE MN

# የCOVID-19 በቤት ውስጥ የሚደረግ ፈጣን ምርመራ አጠቃላይ እይታ፡ iHealth

## በቤት ውስጥ የሚደረጉ ፈጣን ምርመራ መውሰጃ ቦታዎች ምንድን ናቸው?

ማህበረሰብዎን ጤናማ አድርጎ ለማቆየት እና የCOVID-19 ስርጭት ለመቀነስ፣ የMinnesota የጤና መምሪያ (MDH) ነጻ በቤት ውስጥ የሚደረጉ ምርመራዎችን በተጠቀሱ የመውሰጃ ቦታዎች ለሚኒሶታዊያን ለማቅረብ ከአካባቢያዊ የህዝብ ጤና ኤጀንሲዎች፣ የባህላዊ ጤና መሪዎች፣ የምግብ እርዳታ እና ማህበራዊ ነክ ድርጅቶች ጋር አጋር ሆኗል።

## የiHealth የአንቲጅን ፈጣን ምርመራ ምንድን ነው?

iHealth አንቲጅን ምርመራ COVID-19 ን የሚያስከተለውን ቫይረስ ለመለየት ይጠቅማል። ምልክቶች ካሉብዎት፣ ምርመራው በፍጥነት COVID-19 እንዳለብዎት እና እንደሌለብዎት ይነግርዎታል። በማንኛውም ቦታ የአፍንጫ ናሙና በመውሰድ በ15 ደቂቃ ውስጥ ውጤት ማግኘት ይችላሉ።

## የiHealth መቼ መጠቀም እችላለሁ?

የiHealth ምርመራን በማንኛውም ሰዓት በቤትዎ ውስጥ 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት መጠቀም ይችላሉ። የMinnesota የጤና መምሪያ ምርመራውን ለተከታዮቹ ምክንያቶች እንዲጠቀሙ ይመክራል፡

- የCOVID-19 ምልክቶችን እያሳዩ ነው፤
- COVID-19 ካለበት ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበረዎት፤
- COVID-19 ላለበት ሰው ተጋልጠው ከሆነ፤
- ብዙ ሰው በሚሰበሰብበት ቦታ ከመሄድዎ በፊት ምርመራ እያደረጉ ከሆነ።

ምልክቶች ሳይኖርብዎ ምርመራ የሚያደርጉ ከሆነ፣ እባክዎ የiHealth መመሪያዎችን ይከተሉ፣ ወይም የ MDH Close Contacts and Quarantine (www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/close.html)።

## የምርመራ መገልገያውን እንዴት መጠቀም እችላለሁ?

**እባክዎ በምርመራ መገልገያ/ኪት ጥቅል ላይ ያለውን ሙሉ መመሪያ ይከተሉ።** ምርመራው እንዴት እንደሚሰራ ለማወቅ፣ ይህን ቪዲዮ ይመልከቱ፡ How to use the iHealth COVID-19 Antigen Rapid Test (https://youtu.be/qBt_H4Gc-rU)።

## ምልክቶቹ ኖረውብኝ ነገር ግን የiHealth ምርመራዬ ኔገቲቭ ከሆነስ?

የፈጣን ምርመራው ውጤት ኔገቲቭ ቢሆንም፣ ምልክቶቹ የሉበት ሰው የCOVID-19 የ PCR ምርመራ ማድረግ እና ምልክቶቹ ለ24 ሰዓታት ለውጥ እስኪያሳዩ ድረስ ወደ መደበኛ ተግባሩ መመለስ የለበትም። በMinnesota COVID-19 Response (mn.gov/covid19/) የPCR ምርመራ አማራጮችን ያግኙ። ስለ ምልክቶችዎ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ዶክተርዎን ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

## የiHealth ምርመራዬ ፖዘቲቭ ከሆነስ?

ምርመራዎ ፖዘቲቭ ከሆነ፣ ከሌሎች ተለይተው በቤትዎ ይቆዩ። ምልክቶች ካሉብዎት፣ ዶክተርዎን ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ። እዚህ ላይ የሚገኘውን የህዝብ ጤና መመሪያን ይከተሉ If You Are Sick or Test Positive (www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/sick.html)።

## ጥያቄዎች ካሉኝስ ምን ላድርግ?

እባክዎ ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9 a.m. እስከ 7 p.m. ድረስ እና ቅዳሜ ከ10 a.m. እስከ 6 p.m. ክፍት በሆነው የMinnesota የጤና መምሪያ የCOVID-19 የህዝብ የስልክ መስመር ላይ በ1-833-431-2053 ይደውሉ።